ዱንያ ላይ ዕድሜህን ሊያቃጥሉ ከሚችሉ ነገሮች መካከል አንዱ- ለያንዳንዱ ሰው ለማስረዳት ብለህ የምታጠፋው ጊዜ ነው። ከአንዳንድ ነገሮች አንፃር አይተህ እንዳላየህ፣ ሰምተህ እንዳልሰማህ መሆን ግድ ነው። አንዳንዱም እንደሚያልፍ ጥይት ለጥ ብለህ ተኛ። የተኛ ሰው የሚያየውም ሆነ የሚሰማው ነገር አይኖርም። ቢሰድበትም፣ ቢሙቱትም አያመውም፣ ምንም አይሰማውም። እንቅልፍ ውሰጥ የገባ ሰው ሊናደድም፣ ሊበሳጭም። እንቅልፍ ሌላ ዓለም ነው። እዚያ ዓለም ውሰጥ ስትገባ ሁሉን ነገር ትረሳለህ። ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ሲወስድህ...። ከሰው የምላስ ዱላ አንፃር እንቅልፍ ውስጥ መሆንን የመሰለ ነገር የለም። እንቅልፍን የመሰለ ማሸነፊያ ድል የለም። ችግሩ እንቅልፍ አልወስድህ ካለ ነው። በየምቱ የምትታመም ከሆነ ነው። ስለዚህ ብልህ ሁን፤ ምንም እንዳልተፈጠረ ነገር አድርገህ ተጠቅልለህ ተኛ።

አዎ አንደ አስሓበል ከህፍ ሰዎች ዝም ጭጭ በል። ዋሻው ውስጥ ረጅም እንቅልፍ ተኙና ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ድልን ተቀዳጁ። ሲነሱ ያኔ በዘመናቸው ጠላቶቻቸውና አሳዳጆቻቸው የነበሩ ሁሉ ወደ መቃብር ወርደዋል። ሰዎችም ስለነርሱ ረስተዋል። እነርሱ ግን ዛሬም ድረስ ሕያው ናቸው። አንዳንድ ጊዜ መተኛት ግድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። አዎ አንዳንዴ ለወሬዎች ትኩረት ካለመስጠት አንፃር ተኛ አትስማ፤ ተኛ አትይ፤ ተኛ አትናገር። ማየት የምትፈልገውን ብቻ መርጠህ እይ፤ መናገር የምትፈልገውን መርጠህ ተናገር፤ መስማት የምትፈለግውን መርጠህ ስማ። ካልሆነ ተኛ። ያኔ ሰላም ትሆናለህ። መልስ አትስጥ ሰዎች የሚከተሉት መልስህን ነውና።

## 4- ለአላህ ብቻ ብለህ ሥራ

ለአላህ ብሎ የሚኖር ሰው ለሰው ግድ አይኖረውም። ለአላህ ብሎ የሚሠራ ሰው የሰው ነገር ትዝ አይለውም። ግንኙነቱ ሁሉ ከአላህ ጋር ነውና። ዱንያ ላይ ስትኖር ኑሮህን ከአላህ አንፃር ኑር። ሥራህንም ስትሠራ ለአላህ ብቻ ብለህ ሥራ። ስለ አላህ ስትኖር አላህ ይወድሃል፤ ሰዎችም ዘንድ ተቀባይነት ይኖርሃል። ስለ ሰው ስትኖር ግን አላህ ይጠላሃል፤ ሰዎችም አንቅረው ይተፉሃል። ሰዎች ስላንተ ያሉትን ያልሆነ ነገር ስታስብ በትችታቸው አትሸማቀቅ፤ በመልካምነትህ ያወደሱህ እንደሆነም በሙገሳቸው አትመክ። በርግጥ የምትሠራው ለአላህ ከሆነ ሁሉን ነገር፤ ኢድናቆቱንም ትችቱንም እኩል አይ። ያኔ መስመር አትለቅም፤ ሚዛን አትስትም፤ ከፍ ትላለህ፤ ንጉስ ትሆናለህ፤ ታሸንፋለህ። ሰው የሚቆመው በጓደኞቹ ብዛት አይደለም፤ ዋስትናና ድህንነት የሚሆነውም ገንዘቡ አይደለም። የሰው ሰላምና ደህንነቱ ከአላህ ዘንድ ነው፤ እሱ

ይውደድህ ፤ እሱ ሲወድህ ያስወድድሃል ። ስለሆነም ከውጫህ ይልቅ ለውስጥህ ጥሩነት ተጨነቅ።

## 5- ላንተም ለሱም ሰላም ሲባል ምቀኛን ተደበቀው

የቱን ያህል ቢታከሙ ከማይድኑ በሽታዎች መካከል አንዱ ሐሲድ /ምቀኝነት/ ነው። እላህ ይጠብቀን። ሓሲድ ሰው ብቸኛ ችግሩ የሌሎች ማግኘት፣ መሻሻልና መለወጥ ነው። ሓሲድ ሰው በምንም ይሁን በምን እንድትበልጠው አይፈልግም። አንዳንድ ሓሲድ ካንተ የሚፈልገው ብቸኛው ነገር አንተን ምድር ላይ ሰትንቀሳቀስ አለማየት ነው። ካልሆነም ወድቀህ ካላየህ በስተቀር ሰላም የለውም። ወድቀህ አይቶህ ጭምር እንኳን የምትሠራ፣ የምትንቀሳቀስ እየመሰለውም የሚጨነቅ አለ። ስለዚህ ሰላም የምታገኘው ከሱ ስትርቅ ነው። ምቀኝቱን ካወቅከ ላንተም ለሱም ሰላም ሲባል በሱ ዙርያ አጥርህን ከፍ አድርገህ ገንባ። እሱ የራሱን ኑሮ ኖሮ አያውቅም። ኑሮው የሰው ነው። እሱን እርሳና የራስህን ኑሮ ኑር። በሱ የከፋት ሥራና ድርጊትም አትደናገጥ። ወደሱም ዞር ብለህ አትመልከት። ከሱ ጋርም አትሥራ። ከሱ ራቅና በራስህ እጅ ሥራ፣ ትጋ፣ እረስ፣ ዝራ፣ አጠጣ፣ አርም፣ አጨድ።

ሓሲድ ሰው ዐይኑ ጭንቅላቱ ውስጥ ነው። የሚያየውም የሰውን ልብስና ለውጥ ነው ኑሮና ሕይወት ነው። ከምቀኛ ጋር ሰላም ፈጥራለሁ ብለህ አትሞክር። እሱ ለድርድር ዝግጁ አይደለምና። ለምቀኛና ቀናተኛ ጥሩ መሆንን ለማረጋገጥ መድከም አጉል ልፋት ነው። በታመመ ዐይን ነው። አይታውን ማስተካከል አይታሰብም፤ የትኛውም መድኃኒት አይፈውሰውም። ምቀኛ ካለን በልጠናል ማለት ነው። ስለሆነም የበለጠ ነፃ ሆነን ከፍ እንበል።

## 6- ሰውን ለማስደሰት አትድከም

ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታዬ እምላለሁ። የሰውን ልጅ ማስደሰት ፈጽሞ የማይደረስበት ድካም ነው። ልብ በል የቱን ያህል ብታደርግለትም እንኳን አላህ ለሰው ልጅ ያደረገለትን ያህል ልታደርግለት አትችልም። የቱን ያህል ብትሠጠው እንኳን አላህ ለሰው የሠጠውን ያህል የመስጠት አቅሙ የለህም። አላህ የሰው ልጆችን ፈጠራቸው፣ መገባቸው፣ ጤና ሠጣቸው፣ ሲሳይ ሁሉ፣ ሀብት ንብረትም ለገሣቸው። ይህን ሁሉ ኢድርጎላቸው አልተደሰቱበትም፣ አልረኩበትም። ከፊሎቹ ካዱት፣ ሌሎቹ እነወሩት፣ ያመሰገኑትም ቢሆኑ መመስገን ያለበትን ያህል አላመሰገኑትም። ብዙ ኢድርገህልናል

ብለው ጠዋት ማታ አላወደሱትም። እሱ በሥጣቸው ሌላውን ያመሰገኑ በዙ። እሱ በፈጠራቸው ለሌላ የሚሰግዱ በረከቱ። እናም ሰዎችን አስደስታለሁ፤ በነርሱ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት አገኛለሁ ብለህ አትድከም። ድካምህና ልፋትህ ከንቱ ነው የሚሆነው። የቱን ያህል ብታደርግላቸው የሚሉህን አያጡም። ደከመህ ደከመህ መጨረሻ ላይ የሆነ ነገር ይሉሃል፤ በነገር ይወጉሃል፤ ጥላሸት ይቀቡሃል፣ ጥረትህን ሁሉ ያጣጥሉብሃል።

እስቲ ለሰው የምትደከመውን ትንሽ ያህል እጅ ብቻ ለፈጠረህ ጌታ ለአላህ (ሱ.ወ.) ድከም፤ ለአምላክህ ወደቀህ ተነስ፤ በትንሽ ድካም እጅግ ብዙ ትርፍ ታገኝበታለህ።

## 7- በርታ... ጠንክር

ዱንያ ላይ ከመሥራትና ከመበርታት ውጭ አማራጭ የለህም። የሚያበረታታህ ብታጣ እንኳን ራስህን አበርታ። ለራስህ ነዳጅ ሁን፤ ራስህን ግፋ፤ ራስህን ሸልም፤ ለራስህ ተናገር። ሌላውን እንደምትመከረው ሁሉ ራስህንም ምከር -ጎበዝ! በርታ! በል ራስህን። የሆነ ነገር ጀምረህ ሰዎች አይሳካልህም ቢሉህ ያ የራሳቸው፣ የግላቸው አስተያየታቸው መሆኑን አስብ። እነርሱ የራሳቸው አስተያየት እንዳላቸው ሁሉ አንተም የራስህ አቋም ሊኖርህ ይገባል። ያ አቋም የነርሱ ተቃራኒ መሆን አለበት። ንግግራቸውን መስማት የለብህም። መስሚያህን ጥጥ አርገው። ንግግራቸውን ሰማህ ማለት ምኞታቸውን አሳካህ፣ ፍላጎታቸውን አሟላህ፣ ግምታቸውን አፀናህ፣ ለስንፍና እጅ ሠጠህ... ማለት ነው። ስለዚህ የራስህን ሃሳብ አንግስ እንጂ የነርሱን ሃሳብ አታሳካላቸው። አስተያየታቸውን ወደ ሕይወትህ አታምጣ፤ በራስህ ላይ አትተግብር፤ ራስህን አታወናብድ፣ ራስህን አትረብሽ። ማንም የራሱንና የመሰለውን አስተያየት መስጠት ይችላልና ተዋቸው።

ራስህ ካላመንከበት በስተቀር በሰዎች አስተያየት መንገድህን አታቋርጥ። ከሃሳባቸው ከፍ በል፤ ከፍ ብለህም ብረር። መብረሪያ ከንፍህን እንዲቆርጡ፣ ወደታች እንዲጎትቱህ ዕድል አትስጣቸው። ሃሳባቸውን ካላነሳህ፣ ንግግራቸውን ካልሰማህ፣ አስተያየታቸውን ካላዳመጥክ ይሳካልሃል። ማንም ቢናገርህ፣ ቢያሸማቅቅህና ቢሰቅበህ እጅ አትስጥ። ይሳካልኛል በላቸውና ያለድካም ተጓዝ። ትከከለኛው መስመር ላይ እያለህ ተው አይሳካልህም ቢሉህ "አልተውም፤ ያ የናንተ አስተያየት እንጂ የኔ አቋም አይደለም" በላቸው።

## 8- ባለፈው ነገር አትቆዝም

ያለፈ አለፈ። ከሱ ትምህርት አንጂ ምን አይወሰድም። ሞኖ የተቀበረውን ጊዜ እዚህ አምጥተህ አትኑረው። የዛሬውን ሕይወትህን ያሰናከልብሃል፤ የወደፊቱን ዕቅድህን ያበላሽብሃል። ትናንትን አምጥቶ በዛሬው ውስጥ በትናንቱ እሰር ቤት ውስጥ ነው የሚያስቀረው። ሰውን ወደኋላ ይመለሳል፣ ዛሬን ከመኖር ይከለክላል። እናም ትናንትን እዚያው በነበረበት ዝጋበት። የብርሃን ጭላንጭሉም እንዳይወጣ። ለትምህርት ካልሆነ አትከፈተው።

## 9- መውደቅ ወድቆ መቅረት አይደለም

የዱንያ ላይ መሰናከሎች መማርያዎቻችን ናቸውና እንማርባቸዋለን። በሕይወት መንገድ ላይ እከል የገጠመው ሰው ያተርፋል። ብልሆቹ በመከራ በተፈተኑ ቁጥር መውደቅ የለም፤ ወይ መማር አሊያም ማሸነፍ ነው ብለዋል። የዱንያ ሁሉ መንገዷ ዱር ነው። በየትም ተጓዝ መንገዷ አልጋ በአልጋ አይደለም። እከል ካልገጠመህ አገሯ ዱንያ አይደለችም ማለት ነው። መከራ ካልደረሰብህ ትምህርት አላገኘህም ማለት ነው። ባይሆን በጉዞ ላይ የሚያጋጥም ችግር መጠረግ አለበት። ከመንገዱ ላይ መወገድ አለበት። በመሰናከል ምክንያት ከመንገዱና ከጉዞው የቆመ የተሸነፈ ነው። በእከል መቆም መሸነፍ ነው። ወዳጄ አትቁም፤ ለመቆምም አታስብ። መቆም ያለብህ እከል ሲገጥምህ ሳይሆን ስትጨርስ ብቻ ነው። ሳንወድቅና ሳንወጣ ሳንወርድ ከአንድ ቦታ አንደርስም። እውነተኛ ስኬት ልፋት አለው፤ ዙርያ ጥምጥም ነው። ሁሉም እከል የሕይወት አዲስ ገጽ ነው፤ ትንጠለጠልበታለህ። ፌርማታ ነው ነዳጅ ታገኝበታለህ።

## 10-ርቀትህን ጠብቅ

በማኅበራዊ ግንኙነትህ ውስጥ ከሰው ጋር ስትኖር አትጣበቅ። በጣም አትቅረባቸው ይውጡሃል፣ በጣምም አትራቃቸው ይተፉሃል። ለረጅምና ዘላቂ የጓደኝነት ግንኙነት በትስስራችሁ መካከል ክፍተት ተው። ሰውን ስትወድ ውዴታህን በልክ አድርግ። ሰው ሰው መሆኑን እወቅ። መላኢካ አይደለም። በባህሪው ስልቹ ነውና ድንጉት እንዳይገፈትርህ ርቀትህን ጠብቅ። ሰዎች በጣሙን ከቀረብካቸው ያለ ማስጠንቀቂያ ሊያወርዱህም ሊያዋርዱህም ይችላሉ። ያኔ እኔው ነኝ ያበዛሁት፣ የቀበጥኩት፣ ራሴን የጣልኩት ከማለትህ በፊት ርቀትህን ጠብቅ። ትንሽም ብትሆን ለራስህ የምታስቀረው የደህንነት ቀጠና ይኑርህ። ቀልቦች ይቀያየራሉ፤ ስሜቶች ይለዋወጣሉ። ሌላው ራሱን

ችሎና ነፃነቱን ጠብቆ ባለበት ሁኔታ ለሌሎች ባርያ አትሁን። ሙሉነትህ ለሰው አታስረከብ። መጣበቅ ከአላህ ጋር ብቻ ነው።

## 11- በዝምታ ሥራ

አንዳንድ መገለል በተለይ ሥራ ፈት በበዛበት ዓለም ብዙ ትርፍ ያስገኛል። ዛሬ ላይ ሥራ የሚያስፈቱ ነገሮችም ሰዎችም በዝተዋል። ኢንተርኔቱ፣ ዩ ቱዩቡ፣ ቲክቶኩ፣ ሶሻል ሚዲያው፣ የፖለቲካ ወሬው... ሰዎች ረጅም ጊዜ ሰጥተው ሰዓታቸውን የሚፈጁበት ነገር ሆኗል። በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ነቃ በል። በመሃል የሚወስዱህ ነገሮች ቢኖሩ እንኳ ዋናውን ሥራህን አትጣል። ሰዎች በብዛት ስለተጠመዱበትና ስለሠሩት አንድ ነገር መልካም አይሆንም። ባይሆን ከነርሱ ለየት በል። አደፍጥ፤ በዝምታ ሥራ። የሚጠፉትንና የሚያጠፉትን አትከተል። ለዛሬም ለነገም ብዙ ትርፍ ሊያስገኙልህ በሚችሉ ነገሮች ላይ አተኩር።

የሚዲያው ዓለም ባህር ነው። መርካቶ ነው። ሁሉ ነገሩ ይሰባል። ገበያ ነው። ዐይናዋጅ ነው። ያወዛግብሃል፣ ያዘናጋሃል፣ ጠልፎ ያስቀርሃል፣ ስትገባው መውጫ ይጠፋሃል። ከዚህ አንፃር ጠንካራ እና ራሱን መቆጣጠር የሚችል ሰው ሁን። ከገባህም በቀላሉ መውጣት የምትችል ሰው ሁን። በዚህም በዚያም ልብህ አይሰረቅ። የሚስቡና የሚያስፈልጉ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም እጅግ በሚጠቅሙህ ነገሮች ላይ ብቻ አተኩር። ያብለጨለጨ ዕቃ ሁሉ ምርጥ አይደለም። ደምቆ ርዕሱ የተፃፈ ዜና ሁሉ ፍሬ ላይኖረው ይችላል። እናም ጥቂት ብትዘናጋ እንኳ ቶሎ ብለህ ወደ ዋናው ጣቢያህ ተመለስ።

## 12-ያለሜዳህ አትጫወት

ዓሳ ባህር ዓለሙ ነው። አዞ ውሃ ሜዳው ነው። ደረቅ መሬት ላይ ወጥተን ጠላት እንግጠም ቢሉ ሽንፈት ነው የሚከናነቡት። አሞራ አየር ላይ ነው ጨዋታው። ሰማይ ነው መገለባበጫው። መሬት ወርጄ እንደ አባብ በደረቴ እሳባለሁ ቢል እንግልቱ ነው የሚበዛው። ድካሙ ነው የሚያይለው።

አላህ (ሱ.ወ.) ፍጥረታትን ሲፈጥር ቦታ ቦታቸውን አበጀላቸው። የየራሳቸውን መጫወቻ ሜዳ አዘጋጀላቸው። ለአንዱ የገራው ለሌላው ይከብዳል። ለአንዱ የከበደው ለሌላው ይገራል። ሁሉም በየራሱ ሜዳ ሲጫወት ውጤታማ ይሆናል። በማያውቁት

ለየር እና አገር ሄዶ መጫወት፣ መግጠም፣ መፋለም መሸነፍ ነው። ከፍ ሲልም መዋረድ ነው የሚያስከትለው።

እንዲሁ ሁሉ ከሰው ጋር ስትኖርም ሆነ ስትጫወት ሚዳህን ምረጥ። የሚስማማህን የለየር ንብረት እወቅ። በሆነ ቦታ ላይ ለመናገርም፣ ለማሰረዳትም፣ ለመከራከርም መጀመርያ የሜዳውን ባህሪ አስተውል። ዙርያህን ቃኝ። ሰዎቹን አጥና። የዕውቱት ሜዳ ከሆነ ከመናገርህ በፊት ልከህን እወቅ። ጃሂል ሆነህ በአዋቂዎች ውድድር ላይ እትካተፍ። ጅህልና ዕውቱት ሆኖ አያውቅም። ልከን ማወቅ አንዱ የሐያእ ምልክት ነው።

በሆነ ቦታ ላይ ቁጭ ከማለትህ በፊት አዋጭነቱን ገምግም። አትራፊነቱን እይ። ኪሳራው ያመዝናል ብለህ ከፈራህ ለዲንህም ለከብርህም ተጠንቀቅ። ውርደት እንጂ ቅንጣት ተቀባይነት በማይገኝበት ቦታ ላይ አትድከም። ስለ መልካም ነገር ምንነት ላይገባቸው ቀልባቸው ከተደፈነ ጋር አትዳረቅ። ከተገኘህም መልዕክትህን ብቻ አድርሰህ ውጣ። ለሌላ ለብዙ ነገር ሊጠቅም የሚችል ጉልበትህን ማባከን በሌለብህ ቦታ ላይ አታባክን። ንግግር የማትችል ከሆነ የሚችሉትን አስቀድም። ቦታህ ከኋላ ከሆነ ከፊት አትቁም። የመልካም ሥነምግባር ባለቤት ሆነህ ለመልካም እሴቶች ግድ ከሌላቸው ጋር ብትከራከር አይሰሙህም። ከዱርዬዎች ተረብ እገጥማለሁ ብትል መሳቂያ መሳለቂያ ነው የሚያደርጉህ። ከፍንዳታዎች ጋር እሳፈጣለሁ ብትል መቀለጃቸው ነው የምትሆነው።

ልጆችን በልጆች ዐቅል አናግር። ሰዎችን በዕውቀታቸው መጠን ቅረብ። ከውለሞች ፊት ለከርከር አትቅረብ። ችለህ የማትዘጋውን በር አትከፈት፤ መመለሱ የሚከብድህን ቀስት አትወርውር። በማታውቀው እንግዳ በሆንከበት ሜዳ ፍልሚያ አትግባ። ትንገላታለህ፣ ትወድቃለህ፤ ትሸነፋለህ፤ ትዋረዳለህ።

አቅምን አውቆ መኖር ትልቅ ችሎታ ነውና ሁሌም አቅምህን እወቅ፤ ልከህን ተገንዘብ፤ ኢቻህን ለይ።: ወራጆች ባሉበት ስብስብ አትገኝ። ከወረዱት ጋር አትውረድ። ከፍ በልና ሰዎችን ወደራስህ ከፍ አድርጋቸው። ወደራስህ ሳባቸው።

ለሁሉም ጀግና ሜዳ አለው። ለሁሉም ዜጋ አገሩ አለው። የሚመስልህን ፈልግ። ከሚገጥምህ ጋር ተራመድ። ከምትግባባው ጋር ዝመት። ያኔ ነው ውጤታማ መሆን የምትችለው።

## 13-መሬት ሁን... ታጋሽ ሁን

እንደ መሬት ቻይ የለም። ሁሉን ነገር ትችላለች። ከእኩይ እስከ ክፉ፣ ከመናጢ እሰከ ኩሓዲ ሁሉን ነገር ተሸከማለች። ተሸከማማም ዝም ትላለች። እየረገጧት፣ መንጀፊ እየሠሩባት፣ እያጠፉባት ዝም። ዝም ብቻ። ዝምታን የመሰለ ነገር የለም፤ በተለይ መግባባት በከበደበት ቦታ። መቻልን የመሰለ ነገር የለም፤ በተለይ መናገር ነገር በሚያባብስበት ቦታ ላይ። ለሚወረወርበት ድንጋይ ቁብ ሳይሰጥ በዓላማው ቀጥ ብሎ የሚጓዝ ብዙ ርቀት ይሄዳል። በተለይ በዚህ ዘመን፤ ወደፊት የመጓዝ ትልቅ ዓላማ ያለው ሰው የሚወረወርበትን ቀስት ሁሉ መቋቋም የሚችል ሰፊ ደረትና ጠንካራ ትከሻ ሊኖረው ግድ ይላል።

ትዕግስት መራራ ብትሆንም ፍሬዋ ጣፋጭ ነው። ነገሮች ሲከብዱህ፣ ፈተና ሲበዛ፣ የምትኗኗረው ሰው ሲጠፋ ከሰው ራቅ፣ ራስህን አግልል። ዝም በል። አትሰማ፤ አትናገር፤ አትመልስ። መመለስ ካለብህም በሥነምግባርህ ብቻ መልስ። ዝም በል። ነቢያችን ብዙዎችን የማረኩበትና ያስከበሩበት ትልቁ መሣርያቸው ባህሪያቸው ነበር። ሥነምግባራቸው። ብዙን ጊዜ ዝም ይላሉ፤ ይታገሳሉ። መናገር የግድ በሆነበት ቦታ ላይ ብቻ ይናገራሉ። ንግግርህ ያምር ዘንድ ፀባይህ ይመር። ሰዎች ይከተሉህና ይቀበሉህ ዘንድ የነቢዩን ባህሪ ባንተ ላይ ይዩ። ባህሪ ይናገራል፣ ይከራከራል፣ ይገልፃል፣ ያስረዳል ...